# ዜና አመዝኤ



የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ፣ ቅፅ 13 ቁጥር 7 መጋቢት/ሚያዝያ 1999

## በዚህ ዕትም ውስጥ

በመጋቢት እና ሚያዚያ ወራት ከ63 ሺህ ኩንታል በላ የምግብ ዕርዳታ ተሰራጨ።
*ገጽ 2*

የአስቸኳይ ጊዜ የሥነ ምግብ ጥናት የአሰልጣኞች ሥልጠና ተካሄደ።
*ገጽ 3*

በአደጋ መከላልና ዝግጁነት ፖሊሱ መመሪያና ህግ ማሻሻያ ጥናት ሂደት ላይ ውይይት ተካሄደ።
*ገጽ 4*

# የሰብአዊ ዕርዳታ ፍላጎት አጠቃቀም እና መረጃ ልውውጥን ለማሻሻል የተቀናጀ አሠራርን ይበልጥ ማጠናከር እንዳሚያስፈልግ ተገለጸ።

የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ጎትን በመተመን ፣ የተገኘውንም ለተፈለገው ዓላማ በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል እና መረጃ-ችን በወቅቱ በመለዋወጥ ረገድ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲነ በክልል አደጋ መከላከል ቢሮዎች፣ በሚመለከታቸው የፌዴራል መ/ቤቶችና የክልል ቢሮዎች እንዲሁም በረድኤት ሥራ ላይ በተሰማሩ ድርጅቶች መካከል ያለው አሠራር ይበልጥ ማቀናጀትና ማጠናከር እንደሚገባ ተገለጸ።

ይህ የተገለው በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ በተዘጋጀውና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራል መሥሪያ ቤቶች፣ የክልል ቢሮዎች ኋላፊዎችና ተወካዮች



በተገኙበት ሚያዝያ 9 ቀን 1999 ዓ.ም በጊዮን ሆቴል በተንሄደው የጋራ ምክክር መድረክ ላይ ነው። በዚሁ ጊዜ እንደተገለፀው የአደጋ ክስተቶች በሚያጋጥሙበት ጊዜ የሚያስከትሉትን ጉዳት ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ አስፈላጊ የሆኑ ወቅታዊ መረጃዎችን መለዋወጥ ፣ የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታ ፍላጎቶች ለምን ያህል ሕዝብ እና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚያስፈልጉ በማጥናት እንዲሁም የተገኙትን ዕርዳታዎች በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል ረገድ በፌዴራል አመዝኤና በክልል አመዝ ቢሮዎች ፣ በፌዴራል ጤና ጥበቃ ፣ ውሃ ሀብት ልማት እና ግብርናና ገጠር ልማት መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት አካላትና የተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች መካከል የሚኖውን የጋራ ሥራ ግንኙነት ማጠናከርና ማሳካት ከምንም በላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው።

በዚሁ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር አበራ ደሬሳ እና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሜኒስትር ዴኤታ ዶ/ር ከበደ ወርቁን ጨምሮ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል ቢሮ ኋላፊዎችና ተጠሪዎች በተገኙበት የጋራ ምክክር መድረክ ላይ የፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ እንደገለጹት ማንኛውም በሕዝብ ላይ ጉዳት የሚያደርስ የአደጋ ክስተት በአንድ መሥሪያ ቤት ወይም አስፈጻሚ አካል እንቅስቃሴ ብቻ ተፈላጊውን ውጤት ማግኘት ስለማይቻል አደጋዎች

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 5529259
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣ www.dppc.gov.et

ዜና አመዝኤ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲና ተባባሪዎቹ የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዋችንና ሌሎች ተገዳኝ ተግባራትን የሚዘግብ ወርሃዊ ልሳን ነው



በክልል ደረጃ በቁጥጥር ሥር ሊውል የሚችል አደጋን በክልል ባለ ሀብትና የሰው ሀይል ለመቆጣጠር ቁርጠኝነት በማሳየት የዕርዳታ ጠባቂነት ስሜትን ማስወገድ እንደሚገባ በምክክር ስብሰባው ተሳታፊ-ች ተገልጿል፡፡

የሚያስከትሉትን ጉዳት ለመቀነስ ወይም ለማስቀረት የሚመለከታቸው የዘርፍ መሥሪያ ቤቶች ፣ የክልል አስፈጻሚ አካላትና ለጋሾች ከዕርዳታ ፍላጎት ተመን ጀምሮ እስከ አጠቃቀም ድረስ የተቀናጀ ተሳትፎ ማድረግ ወሣኝ እና ሊታለፍ የማይቻል ነው፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ አያይዘውም በተለይ የዘርፍ መሥሪያ ቤቶች በየዘርፎቻቸው የሚያጋጥሙ የዕርዳታ ፍላጎቶችን የመተመኛ መመሪያ በማዘጋጀት ምግብ ነክ ያልሆኑ የአስቸካይ ጊዜ እርዳታ ፍላጎት ጥያቄዎች በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሰረቱ አና ሁሉንም የሚመለከታቸው አካላት በባለቤትነት ስሜት የሚያሳትፉና የሚያንቀሳቅሱ እንዲሆኑ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡ ዋና ዳይሬክተሩ አክለው እንዳሉት የዚህ ዓይነቱን ይበልጥ ወደ እውነታው የተጠጋ የተቀናጀ የአጠናን ሥርዓትን መዘርጋት የጥገኝነት ስሜትን በመቀነስ ዕርዳታውን ለታመለት ተጎጂ በአግባቡ ለማድረስ ያስችላል ብለዋል፡፡

በክልል ደረጃ በቁጥጥር ሥር ሊውል የሚችል አደጋን በክልል ባለ ሀብትና የሰው ሀይል ለመቆጣጠር ቁርጠኝነት በማሳየት የዕርዳታ ጠባቂነት ስሜትን ማስወገድ እንደሚገባ በምክክር ስብሰባው ተሳታፊዎች ተገልጿል፡፡

በተለይ አደጋዎች ሲከሰቱና ከመከሰታቸው በፊት የሚከናወን የዕርዳታ ፍላጎት ትመናን በተመለከተ በተለያዩ ምክንያቶች በሕዝቡ ዘንድ ሰርጾ የሚገኘውን የተረጂነት ስሜት ለማስወገድና ዕርዳታን በአደጋ አካባቢ የወሰነ እና በፍላጎት ላይ ብቻ የተመሠረተ ለማድረግ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት በፌዴራል ደረጃ በተዘጋጁ መድረኮች የሚቀርቡ ሃሣቦች እስከታች መውረድ እንደሚገባቸውና በዚህ ረገድ ተፈላጊውን ውጤት ለማስገኘት ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት በአንድ መንፈስ መንቀሳቀስ እንደሚገባቸው በምክክር መድረኩ ላይ ተንጸባርቋል፡፡

በመጨረሻም የዘርፍ መሥሪያ ቤቶች የሰብአዊ ዕርዳታ እንቅስቃሴን እንደተደራቢ ሥራ ሳይሆን ከዋና ዋና ሥራዎቻቸው እንደአንዱ በመቀበል በስትራቴጂክ ዕቅዶቻቸው ውስጥ ማንተት እንደሚገባቸው ፣ የሚያዘጋ°ዋቸው የሰብአዊ ዕርዳታ ጥያቄዎችም ክልሎችን ፣ የሚመለከታቸው ለጋሾችና መያድን ያሳተፉና በፍላጎት ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ በማድረግ ተአማኒነትን ማጎልበትና ብሎም የሚገኘውን የዕርዳታ ፍላጎት ምላሽ ለማሳደግ የሚጠበቅባቸውን ሚና ለመጫወት ትኩረት ሰጥተው እንዲንቀሳቀሱ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ ለዚህም በተለይ ምግብ ነክ ያልሆኑ የዕርዳታ ፍላጎቶች አጠናን ሥርዓትን የማጠናከርና መመሪያ-ችን በየዘርፎቹ ግብረኋይሎች የማዘጋጀቱ አስፈላጊነቱ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተገልጿል፡፡

## በመጋቢት እና ሚያዝያ ወራት ከ63 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተሰራጨ፡፡

በተለያዩ ክልሎች በደረሱ ድንገተኛ አደጋዎች ሳቢያ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች በመጋቢት እና በሚያዝያ ወራት በጠ ቅላላው 63 ሺህ 710.64 ኩንታል ተሠራጭቶ አብዛኛው ለተጎጂ ወገኖች ተከፋፍሏል፡፡ ከዚሁ በሁለቱ ወራት በየክልሎች ለሚገኙ የአስቸኳይ ጊዜ ተረጂዎች ከተሠራጨው ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 39 ሺህ 191.50 ኩንታል በሚያዝያ ወር መሠራጨቱንና ቀሪው 24 ሺህ 619.14 ኩንታል ደግሞ በመጋቢት ወር የተሠራጨ መሆኑን ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት

ኤጀንሲ የዕርዳታ ፕሮግራሞች መምሪያ የደረሰን መረጃ ያመለክታል በየአካባቢው እንደሚደርሰው የጉዳት መጠንና የተጎጂ ህዝብ ብዛት ከግምት በማስገባት በሚያዝያ ወር ከተሠራጨው 39 ሺህ 191.50 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 963 ኩንታል በምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ጭናክሰን ወረዳ ፣ 5,323.50 ኩንታል በምዕራብ ሸዋ ዞን ግንደ በረት ፣ አድአ በርጋና ሜታ ሮቢ ወረዳዎች ፣ 9,895 ኩንታል በባሌ ዞን አጋርፋና ጋሰራ ወረዳዎች በድምሩ 16 ሺህ 181.50 ኩንታል በኦሮሚያ ክልል ፣ 5161 ኩንታል በአማሮና ቡርጂ ልዩ ወረዳ ፣ 2,777 ኩንታል በዳውሮ ዞን ለቶጫና ማረቆ ወረዳ በድምሩ 9,938 ኩንታል በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ፣ 9 ሺህ 818 ኩንታል በሱማሌ ክልል ምዕራብ ኢሚ ወረዳ ፣ 1030 ኩንታል በሐረሪ ክልል ፣ 491 ኩንታል በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ እና ጠዊ ወረዳዎች እንዲሁም 268 ኩንታል በጋምቤላ ክልል አኝዋ እና ጆር ወረዳ ለሚገኙ ተረጂዎች የተሠራጨ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል::

በተመሳሳይ መልኩ በመጋቢት ወር ከተሠራጨው 24 ሺህ 619.14 ኩንታል ጠ ቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 7 ሺህ 596 ኩንታል ባሌ ዞን ዳዌስረር ወረዳ ፣ 2,483 ኩንታል በኢለባቦር ዞን ጮራና ቦሬቻ ወረዳዎች በድምሩ 10 ሺህ 079 ኩንታል በኦሮሚያ ክልል ፣ 14 ሺህ 494.59 ኩንታል በደቡብ ክልል ቶጫና ማረቆ ወረዳዎች እንዲሁም 45.55 ኩንታል በድሬዳዋ ከተማ ለሚገኙ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ፈላጊዎች የተሠራጨ ነው::

በሚያዚያ ወር ለድሬዳዋ ከተማ ፣ ኦሮሚያ ክልል አጋርፋና ጋሰራ ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ወረዳ እንዲሁም ገምቤላ ክልል አኝዋ ጆር ወረዳ ለሚገኙ ተረጂዎች የተሠራጨውና እየተሰራጨ የሚገኘው የምግብ ዕርዳታ ለተረጂዎቹ ለግንቦት ወር ያስፈልጋል ተብሎ የተተመነውንም ጭምር የሚያካትት እንደሆነ ከዕርዳታ ፕሮግራሞች አፈጻጸም ክትትል መምሪያ ያገኘነው መረጃ ያስረዳል::

በተለያዩ ክልሎች በደረሱ ድንገተኛ አደጋዎች ሳቢያ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች በመጋቢት እና በሚያዝያ ወራት በጠ ቅላላው 63 ሺህ 710.64 ኩንታል ተሠራጭቶ አብዛኛው ለተጎጂ ወገኖች ተከፋፍሏል::



## የአስቸኳይ ጊዜ የሥነ ምግብ ጥናት የአሰልጣኞች ሥልጠና ተካሄደ::

በአስቸኳይ ጊዜ የሥነ-ምግብ ጥናት ላይ ለተሰማሩ ቁጥራቸው 22 ለሚሆኑ የፌዴራልና ከ5 ክልሎች ለተውጣጡ ባለሙያዎች ከመጋቢት 10 እስከ 21 ቀን 1999 ዓ.ም የአሰልጣኞች ሥልጠና ተሰጠ:: ይኸው ደረጃውንና ጥራቱን የጠበቀ የሥነምግባዊ መረጃ ለመሰብሰብ ፣ ለመተንተንና የተሰበሰቡ የመረጃ ቋቶችን /ዳታዎች/ በፌዴራል ፣ በክልልና በወረዳ ደረጃ ለመተርጎም የሚያስችል አቅምን ለመገንባት ታስቦ በተዘጋጀው በዚሁ

የአሠልጣኞች ሥልጠና ላይ ፣ደረጃውን የጠበቀ የሥነ-ምግብ ጥናት መረጃ ስለመሰብሰብና ትንተና ማካሄድ በሚሉና ሌሎች ተዛማጅ ርዕሶች ዙሪያ በባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል::

ከፌዴራል ፣ ከክልልና ከወረዳ የጤናና የግብርና ገጠር ልማት ጽ/ቤቶች የተውጣጡ ባለሙያዎች በተሳተፉበት በዚሁ ሥልጠና ላይ በገለፃ ፣ በውይይትና በመስክ በታገዘ የአንድ በአንድ ጥናትና ተሞክሮ ላይ ያተኮረ ትምህርት ለሰልጣኞቹ መስጠቱ ታውቋል::

ሰልጣኞቹም ወደ መደበኛ ሥራቸው በሚመለሱበት ወቅት የቀሰሙትን ትምህርት በየደረጃው ላሉ አካላት በማስተላለፍ በቅድሚያ ማስጠንቀቂያና በሥነ-ምግብ መረጃዎች አሰባሰብ ፣ አተናተንና አተረጓጎም ረገድ ያለውን የአቅም ችግር ያቃልላሉ ተብሎ ይጠበቃል::

## በአደጋ መከላልና ዝግጁነት ፖሊሲ መመሪያና ህግ ማሻሻያ ጥናት ሂደት ላይ ውይይት ተካሄደ::



በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፖሊሲ መመሪያና የህግ ማሻሻያ ጥናት ሂደት ላይ ያተኮረና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የመንግሥት ፣ ለጋሽና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ልዩ ልዩ አካላትን ያሳተፈ የግማሽ ቀን ውይይት ተካሄደ::

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፖሊሲ መመሪያና የህግ ማሻሻያ ጥናት ሂደት ላይ ያተኮረና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የመንግሥት ፣ ለጋሽና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ልዩ ልዩ አካላትን ያሳተፈ የግማሽ ቀን ውይይት ተካሄደ::

የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስልት ፣ በመንግሥት ተቋሞች ለአደጋ መከላልና ሥራ አመራር ዘረፈ ብዙ አደጋዎችን ለመለየት የሚያስችል የካርታ ዝግጅትና የአቅም ግንባታ ፍላጎት ጥናቶች መካከል አንዱ ነው::

አገሪቱ ለአደጋዎች ስትጋለጥ ረጅም ጊዜ ያሳለፈች መሆኑን ያስታወሱት ዋና



ሚያዝያ 2 ቀን 1999 ዓ.ም በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አዳራሽ በተካሄደውና ከ25 በላይ የባለድርሻ አካላት ተጠሪዎችና ተወካዮች በተሳተፉበት በዚሁ ውይይት ላይ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ሲሞን መቻለ እንደገለፁት የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲና በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) ትብብር ከሚካሄዱት የአስቸኳይ ጊዜ ዝግጁነት ማጠናከሪያ ፕሮጀክት ፣ በኑሮ መሠረቶች ላይ የተመረኮዘ ብሄራዊ

ዳይሬክተሩ መንግሥት በአደጋ የተጎዱ ዜጎችን ለመርዳት ከፍተኛ ሚና ሲጫወት መቆየቱና ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ እንደሚገኝ አያይዘው ገልፀዋል::

አያይዘውም ይህንኑ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የሚያስከትሉትን ጉዳት ለመቀነስና ለመከላከል እየተሠራበት ያለውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፖሊሲና መመሪያዎችን በማሻሻል ጊዜው ከሚጠይቀው የአደጋ መከላከልና ሥራ አመራር ጋር የተቀናጀ

ፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ ማዘጋት አስፈላጊ መሆኑን በማጤን የሁልጊዜ ተባባሪዎች ከሆኑት የአሜካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) ፣ የእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የልማትና የዕርዳታ ድርጅት (DFID) እና በኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ልዩ ልዩ አካላት ትብብርና ድጋፍ ጥናቱ እየተካሄደ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል፡፡

የውይይቱ ተሳታፊዎች ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲና ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ የተውጣጡ ባለሙያዎችን ባቀረቧቸው የብሔራዊ አደጋ መከላከል ሥራ አመራር ፖሊሲና መመሪያዎችን ፣ አግባብ ያለውን የህግ ማሻሻያ ሀሳብን ለአደጋ መከላከልና ሥራ አመራር የተቀናጀ ሥራ ለማካሄድ የሚመለከታቸውን መሥሪያ ቤቶች አቅም ለማጠናከርና ለአደጋ ቅነሳ የሚረዳ ችሎታ ማሳደግን እንዲሁም የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲና ሌሎች ተመሳሳይ ተልዕኮ ላላቸው መሥሪያ ቤቶች አቅም ማጠናከርንና ተደጋጋሚ በሆኑትና በቀላሉ ሊተነበዩ በማይችሉ አደጋዎች መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ የሚችሉበትን አቅም ማሳደግን በተመለከተ የፖሊሲና የመመሪያ ርዕሰ ሃሳቦችን ለማግኘት ተችሏል፡፡ ወደፊትም ተመሳሳይ ውይይቶች በማካሄድ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፖሊሲ ማሻሻያ ጥናቱ ይበልጥ የሚዳብርበት ስልት መቀየሱንም የኤጀንሲው የፖሊሲ ኘላንና ፕሮግራም መምሪያ አስታውቋል፡፡